መልእክት አሥራ-ሁለት

**በጌታ ምለሳ የሕይወትን መንገድ መውሰድ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ሩት 1፡16-17፣ 20-21፤ 2፡10-16፤ 3፡1፣ 7-13፤ 4፡9-15፤ ማቴ. 7፡13-14

**I. የኢያሱ፣ የመሣፍንት እና የሩት ሦስቱ መጻሕፍት የእግዚአብሔርን እንቅስቃሴ ሁለት ገጽታዎችን ግልጽ ስዕል ያቀርቡልናል፡- በገቢራዊው መንፈስ የሆነውን እንቅስቃሴውን እና በሕይወት መንፈስ፣ በሕላዌያዊ መንፈስ የሆነውን እንቅስቃሴውን—መሣ. 13፡25፤ 14፡6፤ ዮሐ. 20፡22፤ ሐዋ. 1፡8፤ ሮሜ 8፡2፡-**

ሀ. በኢያሱ፣ ካሌብ እና በመሣፍንቶቹ በሙሉ በኃይል የሆነውን የእግዚአብሔርን እንቅስቃሴ እናያለን፣ ይህ ደግሞ በሕይወት መንፈስ ሳይሆን በኃይል መንፈስ እንደተንቀሳቀሰ ሰው በሶምሶን እንደምሳሌ እናያለን—መሣ. 14፡6።

ለ. በተቃራኒ የሩት መጽሐፍ የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ስለ ኃይል ምንም አይነት ነገር ሊነግረን ሳይሆን ኑኃሚንን፣ ሩትን እና ቦዔዝን በመጠቀም የሕይወትን ነገሮች ፈጽሞ የሚገልጥ ነው—1፡16-17፣ 20-21፤ 2፡10-16፤ 3፡1፣ 7-13፤ 4፡9-15።

ሐ. በጌታ ምለሳ ውስጥ ኃይለኛ ለመሆን እና ታላቅ ሥራ ለመሥራት የመሣፍንትን መንገድ መውሰድ የለብንም፤ በሕይወት መንገድ ምትክ የኃይልን መንገድ ከወሰድን የምናከናውነው ነገር በሙሉ ትርጉም አይኖረውም።

መ. ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ሊያመጣ እንደሚችል ማየታችን ወሳኝ ነው—ሉቃ. 1፡35፡-

1. እግዚአብሔርን ወደ ሰብዕና ውስጥ ሊያመጣ፣ ክርስቶስን ሊያፈራ፣ ክርስቶስን ለሌሎች ሊያገለግል እና መላውን የሰው ዘር በክርስቶስ አቅርቦት ሊሞላ የሚችለው ሕይወት ብቻ ነው—ማቴ. 1፡18፣ 20-21።
2. ይህ የሕይወት ሰዎች በነበሩት፣ የሕይወትን መንገድ በወሰዱት በሩት እና በቦዔዝ ተከናወነ።

**II. በመለኮታዊው እና ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ሕይወት ባሕርይ መሠረት የእግዚአብሔር ሕይወት ልዩና ብቸኛው ሕይወት ነው፤ የእግዚአብሔር ሕይወት ብቻ እንደ ሕይወት ሊቆጠር ይችላል—ዮሐ. 1፡4፤ 10፡10፤ 11፡25፤ 14፡6፡-**

ሀ. ሕይወት ምሥጢራዊ ነው፣ ምክንያቱም ሕይወት እግዚአብሔር ራሱ ነው—1፡1፣ 14፤ 5፡26፤ ኤፌ. 4፡18፡-

1. መለኮታዊው ሕይወት እንደ የእግዚአብሔር የመጀመሪያው እና መሠረታዊው ባሕርይ ሊቆጠር ይችላል—ቁ. 18፤ ዮሐ. 5፡26፤ 1 ዮሐ. 5፡11-12፤ ሮሜ 8፡2።
2. ሕይወት የእግዚአብሔር ይዘት እና የእግዚአብሔር መፍሰስ ነው፤ የእግዚአብሔር ይዘት የእግዚአብሔር ማንነት ነው፣ የእግዚአብሔር መፍሰስ ደግሞ የእግዚአብሔር ራሱ እንደ ሕይወት ለእኛ መካፈሉ ነው—ኤፌ. 4፡18፤ ራእ. 22፡1።
3. ሕይወት ክርስቶስ ነው፣ እና ሕይወት ክርስቶስ በእኛ ውስጥ መኖሩና ከውስጣችን ወደ ውጭ መኖሩ ነው—ዮሐ. 14፡6፤ ቆላ. 3፡4፤ ገላ 2፡20፤ ፊልጵ. 1፡21።
4. ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ነው—ዮሐ. 14፡16-17፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ሮሜ 8፡2፤ 2 ቆሮ. 3፡6።
5. ሕይወት በሂደት ያለፈው እና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ወደ እኛ ውስጥ መታደሉ እና በእኛ ውስጥ መኖሩ ነው—ዮሐ. 1፡14፤ 7፡37-39፤ 20፡22፤ ሮሜ 8፡10፣ 6፣ 11።

ለ. እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ እና በምሳሌው በመፍጠሩ ውስጥ የነበረው የእግዚአብሔር ዓላማ፣ ሰው የሕይወት ሰው፣ አምላክ-ሰው እንዲሆን እግዚአብሔርን በባሕርያቱ ይገልጠው ዘንድ እግዚአብሔርን እንደ ሕይወት እንዲቀበለው ነበር—ዘፍ. 1፡26፤ 2፡9።

**III. ክፉንና መልካምን የሚያስታውቀውን የእውቀት ዛፍ ትርጉም ማወቅ እና ሙሉ በሙሉ ከዚህ ዛፍ ሕይወት ወደሚሰጠው ዛፍ መዞር ያስፈልገናል—ቁ. 9፣ 16-17፡-**

ሀ. የሕይወት ዛፍ ሦስታንዱን አምላክ በክርስቶስ ያመለክታል፣ ወደ ተመረጡት ሕዝቡ በምግብ መልክ ራሱን እንደ ሕይወት ለማደል—ቁ.9።

ለ. ክርስቶስ የሕይወት ዛፍ ስዕል መፈጸም እንደሆነ አዲስ ኪዳን ይገልጣል—ዮሐ. 1፡1፣ 4፣ 14፤ 11፡25፤ 14፡6፤ 15፡1፣ 5፡-

1. ዮሐንስ 1፡4 ስለ ክርስቶስ ሲናገር "በእርሱም ሕይወት ነበረች" ይላል፤ ይህ በሕይወት ዛፍ የተመሰለውን ሕይወት ያመለክታል።
2. በዘፍጥረት 2 የተሳለው ሕይወት በክርስቶስ ሥጋ የለበሰው ሕይወት ነው—1 ዮሐ. 5፡11-12፤ ዮሐ. 1፡1፣ 4፣ 14።
3. ዮሐንስ 1፡4ን እና 15፡5ን በአንድ ላይ ስናደርጋቸው ሕይወት እና የወይን ዛፍ የሆነው ክርስቶስ ራሱ፣ የሕይወት ዛፍ እንደሆነ እንገነዘባለን።

ሐ. ክፉውን እና መልካሙን የሚያስታውቀው የእውቀት ዛፍ ለሰው ሰይጣንን እንደሞት ምንጭ ያመለክታል—ዕብ. 2፡14፡-

1. መልካሙን እና ክፉውን የሚያሳውቀው የእውቀት ዛፍ ከእግዚአብሔር ውጭ የሆኑትን ነገሮች በሙሉ ያመለክታል።

2. መልካም ነገሮች እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ኃይማኖታዊ የሆኑ ነገሮች ሳይቀሩ፣ እግዚአብሔር ራሱ ያልሆነውን ነገር በሙሉ አሳቹ ሰይጣን ሞትን ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማምጣት ሊጠቀምባቸው ይችላል—ማቴ. 16፡18፤ ምሳ. 16፡25፤ 18፡21።

መ. በዮሐንስ 4፣ 8፣ 9 እና 11 ውስጥ ክፉን እና መልካምን በመጻረር የሕይወትን መርህ የሚያሳዩ አራት ክስተቶች አሉ፡-

1. ለሕይወት እንጂ ለመልካም ሆነ ለክፉ ግድ መሰኘት የለብንም—4፡10-14፣ 20-21፣ 23-24፤ 8፡3-9፤ 9፡1-3፤ 11፡20-27።
2. አንድን ጉዳይ የመለየት ምርጡ መንገድ በሕይወት ወይም በሞት መሠረት እንጂ ነገሩ ትክክል ከመሆኑ ወይም ካለመሆኑ፣ መልካም ወይም ክፉ ከመሆኑ አኳያ አይደለም—ሮሜ 8፡6፤ 2 ቆሮ. 11፡3።

## IV. ክርስቶስ ሕይወታችን ነው—ቆላ. 3፡4፡-

ሀ. የእግዚአብሔር ሕይወት የክርስቶስ ሕይወት ነው፣ የክርስቶስ ሕይወት ደግሞ ሕይወታችን ሆኗል—ቁ. 4፤ ዮሐ. 5፡26፡-

1. ክርስቶስ ሕይወታችን መሆኑ ትርጉሙ ለእኛ ክርስቶስ ፈጽሞ ልምምዳዊ መሆኑ ነው—1፡4፤ 14፡6፤ 10፡10፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ሮሜ 8፡10፣ 6፣ 11፡-
2. አንድን ማንነት፣ ከዛ ማንነት ሕይወት መለየት አይቻልም፣ ምክንያቱም የአንድ ማንነት ሕይወት ያ ማንነት ራሱ ነው፤ ስለዚህ ክርስቶስ ሕይወታችን ነው ማለት ክርስቶስ እኛን ሆኗል፣ እና ከእርሱ ጋር አንድ ሕይወት እና አንድ ኑሮ አለን ማለት ነው—ዮሐ. 14፡6፤ ፊልጵ. 1፡21።

ለ. ክርስቶስ ሕይወታችን የመሆኑ እውነት፣ እርሱን እንደ ሕይወት መውሰድ እንዳለብን እና በየዕለት ኑሯችን እርሱን መኖር እንዳለብን ጠንካራ አመልካች ነው—ቆላ. 3፡4፤ ዮሐ. 6፡57፡-

1. በተግባራዊ እና በልምምዳዊ መንገድ ክርስቶስ ሕይወታችን መሆን አለበት፤ ዕለት ዕለት በሕይወቱ መዳን ያስፈልገናል—ቆላ. 3፡4፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ሮሜ 5፡10።
2. አዲሱ ሰው ክርስቶስን እንደ ሕይወታችን እና እንደ ኑሯችን የመውሰዳችን ቅጽበታዊ ውጤት ነው—ቆላ. 3፡3-4፣ 10-11።

## V. በእግዚአብሔር ፊት ሕይወታችንን እና ሥራችንን በተመለከተ ሁለት አማራጭ መንገዶች አሉ፡- ወደ ሕይወት የሚመራው መንገድ እና ወደ ጥፋት የሚመራው መንገድ—ማቴ. 7፡13-14፡-

ሀ. ወደ ሕይወት የሚወስደውን መንገድ ለመውሰድ በጠባቡ ደጅ መግባት እና በቀጭኑ መንገድ መጓዝ ያስፈልገናል—ቁ. 13-14፡-

1. ጠባቡ ደጅ ውጫዊ ባሕሪያችንን ብቻ ሳይሆን ውስጣዊ አነሣሽ ምክንያታችንን ጨምሮ ያስተካክላል።
2. አሮጌው ሰው፣ እኔነት፣ ሥጋ፣ ሰዋዊ ጽንሰሃሳብ እና ዓለም ከክብሯ ጋር እነዚህ ሁሉ ተወግደዋል፤ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚመጥኑት ነገሮች ብቻ በዚህ መንገድ ውስጥ መግባት ይችላሉ—ቁ. 21፤ 12፡50።
3. መጀመሪያ በጠባቡ ደጅ እንገባለን፣ ከዚያም የሕይወት ዘመናችንን ሁሉ በሚወስደው እና ወደ ሕይወት በሚመራው መንገድ፣ በቀጭኑ መንገድ እንራመዳለን—7፡14።
4. በማቴዎስ 7፡14 ሕይወት የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሕይወት የተሞላውን የመንግሥቱን ዘላለማዊ ብሩክ ሁኔታ ነው፤ ይህ ሕይወት ዛሬ በመንግሥቱ እውነታ ውስጥ ነው፣ በሚቀጥለው ዘመን ደግሞ የመንግሥቱ መገለጥ ይሆናል—19፡29፤ ሉቃ. 18፡30።

ለ. ተፈጥሯዊ ጣዕሞችን በማርካት ሕዝብን ያስደስት ዘንድ፣ የሰውን ሙያ ያስጠብቅ ዘንድ እና የሰውን ፕሮጀክት ያሳካ ዘንድ ደጁ ሰፊ የሆነው መንገድ በዓለማዊ ሥርዓቶች መሠረት ነው፤ ሰፊው መንገድ የሚያስከትለው ጥፋት የሰውን መጥፋት የሚያሳይ ሳይሆን የሰውን ድርጊቶች እና ሥራዎች ጥፋት የሚያሳይ ነው—1 ቆሮ. 3፡15፤ ማቴ. 13፡31-33፤ ራእ. 2፡13፣ 20፤ 17፡4-5።

ሐ. የጌታ ምለሳ መንገድ በሚቀጥለው ዘመን በመንግሥተ ሰማያት መገለጥ በሕይወት ሕያው ወደሆነ ሽልማት የሚመራ የሕይወት መንገድ ነው—መዝ. 16፡11፤ ኤር. 21፡8፤ ማቴ. 19፡29፤ ሉቃ. 18፡30፤ 1 ቆሮ. 3፡13-15፤ 15፡58።

## VI. በሕይወት ስሜት—በውስጣችን ባለው የመለኮታዊው ሕይወት ስሜት፣ ንቃተ-ሕሊና መኖር ያስፈልገናል—ሮሜ 8፡6፤ ኤፌ. 4፡18-19፡-

ሀ. የሕይወት ስሜት ምንጭ መለኮታዊው ሕይወት፣ የሕይወት ሕግ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ በውስጣችን የሚኖረው ክርስቶስ እና እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ መሥራቱ ነው—ሮሜ 8፡2፣ 10-11፤ ፊልጵ. 2፡13።

ለ. መለኮታዊው ሕይወት ብልጡግ፣ እጅግ ጠንካራ እና እጅግ በጉጉት የተሞላ ስሜት ያለው ከፍተኛው ሕይወት ነው፤ ይህ ስሜት የሕይወት ስሜት ነው—ኤፌ. 4፡18።

ሐ. በመለኮታዊው ሕይወት ወይም በተፈጥሯዊው ሕይወት፣ እና በሥጋ ወይም በመንፈስ እየኖርን መሆናችንን እናውቅ ዘንድ በማድረግ የሕይወት ስሜት ይመራናል፣ ያስተዳድረናል፣ ይቆጣጠረናል እንዲሁም አቅጣጫ ያስይዘናል—ሮሜ 8፡6።

**VII. ቤተ ክርስቲያን ላይ በሚነጣጠር የሞት ጥቃት ላይ ድል መንሳት እና በክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት የክርስቶስን አካል መገንባት ያስፈልገናል—ማቴ. 16፡18፤ ዮሐ. 11፡25፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 4፡16፦**

ሀ. በመንፈሳችን ውስጥ ባለው በክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት በቤተ ክርስቲያን ላይ በሚነጣጠረው የሞት ጥቃት ላይ ድል መንሳት እንችላለን—ማቴ. 16፡18፤ ሐዋ. 2፡24፤ 2 ጢሞ. 1፡10፦

1. ከኤደን ገነት ጀምሮ እግዚአብሔር ከሰይጣን ጋር ያለው ውዝግብ በሕይወት እና በሞት ጉዳይ ላይ ሆኗል—ሮሜ 8፡6፣ 10-11፤ ዕብ. 2፡15።
2. ማቴዎስ 16፡18 በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚነጣጠረው ጥቃት ከየት እንደሚመነጭ—"ከገሃነም ደጆች"፣ ማለትም ከሞት እንደሚመነጭ ያሳየናል፤ የሰይጣን ልዩ ዒላማ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሞትን ማሰራጨት ነው፣ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ የእርሱ ታላቁ ፍርሃት ደግሞ የእርሱን የሞት ኃይል መቋቋሚ ነው—ራእ. 2፡8፣ 10-11።

ለ. በክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት የክርስቶስን አካል ለመገንባት መንፈሳችን መንቀሳቀስ አለበት—ኤፌ. 2፡6፣ 21-22፤ 4፡16፤ ራእ. 1፡18፤ 2፡8፤ ፊልጵ. 3፡10፦

1. እንደ የክርስቶስ አካል የቤተ ክርስቲያን ባሕርይ ትንሣኤ ነው፣ የትንሣኤ እውነታ ደግሞ ሕይወት-እንደሚሰጥ መንፈስ ክርስቶስ ነው—ዮሐ. 11፡25፤ ሐዋ. 2፡24፤ ኤፌ. 1፡19-23፤ 1 ቆሮ. 15፡45።
2. በውስጣችን ባለው የመለኮታዊው ሕይወት ስንኖር ለክርስቶስ አካል መገንባት በትንሣኤ የሆነ ሕይወት እየኖርን ነው—ፊልጵ. 3፡10-11፤ ኤፌ. 4፡15-16፤ ቆላ. 2፡19፤ 3፡15።

**VIII. "እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን"—1 ዮሐ. 3፡14፦**

ሀ. ሞትን በሚያመጣው መልካሙንና ክፉውን በሚያሳውቀው የእውቀት ዛፍ የተመሰለው ሞት ከእግዚአብሔር ጠላት ከዲያቢሎስ ነው—ዘፍ. 2፡9፣ 17።

ለ. ሕይወትን በሚያመነጨው በሕይወት ዛፍ የተመሰለው ሕይወት የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ነው—ቁ. 9፣ 16-17።

ሐ. ሞት እና ሕይወት ከሁለት ምንጮች፣ ማለትም ከሰይጣን እና ከእግዚአብሔር ብቻ አይደሉም፤ በተጨማሪም ሁለት ውስጠ-ነገሮች፣ ሁለት ንጥረ-ነገሮች እና ሁለት ክበቦች ናቸው—ዮሐ. 5፡24።

መ. ከሞት ወደ ሕይወት መሻገር ከሞት ምንጭ፣ ውስጠ-ነገር፣ ንጥረ-ነገር እና ክበብ ወደ ሕይወት ምንጭ፣ ውስጠ-ነገር፣ ንጥረ-ነገር እና ክበብ መሻገር ነው፤ ይህ የተከናወነው ዳግም በተወለድንበት ጊዜ ነበር—1 ዮሐ. 3፡14፤ ዮሐ. 3፡3፣ 5፣ 15።

ሠ. ወንድሞችን ስለምንወድ ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እናውቃለን—የውስጥ ንቃተ-ሕሊና አለን፤ ለወንድሞች ያለን ፍቅር (የእግዚአብሔር ፍቅር) ለዚህ ጠንካራ ማረጋገጫ ነው—1 ዮሐ. 3፡14፦

1. በጌታ ማመናችን ከሞት ወደ ሕይወት ለማለፋችን መንገዱ ነው፤ ለወንድሞች ያለን ፍቅር ከሞት ወደ ሕይወት ለመሻገራችን ማረጋገጫ ነው—ዮሐ. 5፡24፤ 1 ዮሐ. 3፡14።
2. ማመን የዘላለምን ሕይወት መቀበል ነው፤ ፍቅር በዘላለማዊው ሕይወት መኖር እና የዘላለምን ሕይወት መግለጥ ነው—ዮሐ. 3፡15፣ 36፤ 1 ዮሐ. 3፡11፣ 14-18፤ 4፡7-12፣ 16፣ 19-21።

© 2021 Living Stream Ministry